# የክርስቶስ መመለስ ራእይ

(The Vision of the Return of Christ)

(በዳዊት ሚካኤል)
(by David Michael)

(ኢሳይያስ 63፥1) እንዲህ ይላል፡ *ይህ ከኤዶምያስ፥ ልብሱም የቀላ ከባሶራ [በኤዶሚያስ ውስጥ] የሚመጣ፥ አለባበሱ ያማረ፥ በጕልበቱ ጽናት የሚራመድ ማን ነው? በጽድቅ የምናገር [ነፃነትን የሚያውጅ] ለማዳንም የምበረታ እኔ ነኝ።*

እንዲሁም በ(እንባቆም 3፥3-15) *እግዚአብሔር ከቴማን (የመን)፥ ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል። ክብሩ ሰማያትን ከድኖአል፥ ምስጋናውም ምድርን ሞልቶአል። ፀዳሉም እንደ ብርሃን ነው፤ ጨረር ከእጁ ወጥቶአል፤ ኃይሉም በዚያ (በመቅደሱ) ተሰውሮአል።* (እባካችሁ ቀሪውን ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ አግኝታችሁ አንብቡት።) ኢሳይያስ 34፥9፤ መዝሙር 110፤ መዝሙር 45፤ ራእይ 19፤ ይሁዳ 14፣15

ዳዊት ያየውና ያሳለፈው ነገር በጣም ድንቅ ነበር። የ**ጌታ** ኢየሱስን መመለስ አይቷል፥ ከቴማን (የመንና ሳኡዲ አረቢያ) በላይ ባለው ሰማይ ውስጥ አልፎ ከሰማይ ወደ ምድር ህዋ የወረደው። ከ**ጌታ** ጋር ወደ ላይ መወሰድና ከ**እ**ርሱ ጋር በአየር ውስጥ መመለስ ምን እንደሚመስል ቃልበቃል አስቀምጦታል። **እ**ርሱ እንደሰጠኝ ከእናንተ ጋር ልካፈለው እሞክራለሁ፥የሚቻል ይመስል።

*ገጠመኙ ሲከፈት ወደ ሌላ ቦታ እንደሚወሰድ ዓይነት ተሰማኝ። ዙሪያዬን ተመለከትሁና በዙሪያዬ የተሰበሰቡትን አየሁ፥ የማይቆጠር መጠን ያላቸው ቅዱሳን። ፊታቸው የተዋበና የሚያበራ ነበር፥ በዚያም ያሉት ለበጉ ሠርግ እራት ነበር። ሙሽራው፥ እኔም ተካፋይ (አካል) የሆንሁበትና ከ**እ**ርሱ ጋር በአየር ላይ ለመሆን በመቅደሱ እየተንሳፈፍሁ የተነጠቅሁበት፥ በጣም በከፍታ ከአረቢያ (Arebian Peninsula) ሰማይ በላይ። በመለኮታዊ የሙሽራ ከለላ ጥላ ስር ተሰውረን ነበር። ዙሪያዬን ስመለከት፥ ከዚህ በፊት ካየሁት ከማንኛውም ነገር በሚበልጥ ሕንፃ ውስጥ ነበርሁ። ሰፊም ረዥምም ነበር። ኮርኒሱ ረዥም ከመሆኑ የተነሳ ሕንፃው በምድር ላይ የተሠራና የሆነ ሰው ከጎረቤት ሀገር ሆኖ እንደሚያየው ይመስላል። አንድ ሰው ከጥንት ጀምሮ እስከ ታላቁ የቤተክርስቲያን መነጠቅ ድረስ ያሉ ቅዱሳንን ለመያዝ የተሠራን ሕንፃ ግዝፈት ሊገምት ይችላል። (*[1ተሰ.4:16](1ተሰ.4:16) ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።*)*

*ወደ ላይ ስመለከት፥ በድንገት መጋረጃው ተገለጠና **መሢሕን** በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በአግራሞትና በደስታ ፍጹም የሆነችውን ሙሽራውን እየቃኘ አየሁት። የ**መሢሑ** ዓይኖች ወደ ታላቁ የቅዱሳን ማህበረሰብ በቀስታ አያየ፥ በጥልቀትና ዘልቆ በሚገባ እይታ ወደ ሁሉም ዓይኖች ይመለከታል፥ በትሑት ፍቅሩ ነፍሳቸውን እየማረከና እያጽናና። በእኔ እንደዚህ ነበር። ዓይኖቻችን ሲገጣጠሙ፥እሺታውን አገኘሁ፥ከእርሱ ጋር በዚያ በመሆኔ ታላቅ ደስታውን። ለእኔና በምድር ላለችው ቤተክርስቲያን ያለውን ታላቅ ክብደት ያለውን ዓላማውን ማየትና መረዳት እችል ነበር። ከዛው ጋር የዘላለም ሕይወትን መረዳትም ነበረኝ። የተትረፈረፈ ሀሴት ልቤን ሞላው። ያ ሁሉ አሁን እንደምረዳው ህያው በሆነው ደስታና ሀሴት ላይ ስለጨመረ ጥልቅ የሆነ ምስጋና። የተሟላና አስደሳች ድግስ፥ አስደሳችና አዝናኝ ክስተቶች፥ የሙሽሮች ዜማ፥ የሙሽሪት ሽብሽባ (ውዝዋዜ) ሁሉ የዚህ ረዥም ጊዜ የተጠበቀ ከ**ወዳጃችን** ጋር የሚደረግ ጥልቅ ቁርኝት ጊዜ ነበር። በመጨረሻ፥ እኛ እንደታወቅን **እ**ርሱን ደግሞ አወቅነው። ምናልባት ደቂቃዎች በነበረ ሁኔታ፥ የፍቅር መሟላት ልብ ፊጽሞ ሊዘጋጅ ከሚችለው በላይ ነበር። ሊሰማኝ የምፈልገው ወይም እንዲሰማኝ ልመኘው ተስፋ የማደርገው ነገር ሁሉ ውስጤ እየፈነዳ ነበር። በግሩም እርካታ በ**እ**ርሱ ላይ ተተክዬ ነበር። መለኮታዊ ፍቅር ጥልቅ ማንነቴና እየተቆጣጠረውና በመደነቅና በመገረም ጠርጎ እየወሰደኝ ነበር።*

እንደዛም ሆኖ፥ በፍቅሩ እንደ ትንሽ ባጠረችው በዚህ አስደናቂ ቅጽበት ውስጥ እንኳን፥ በሚቃኙና በርኅራኄ በትኩረታዊ ምልከታው ላይ አተኩረን ለማወቅ የምንሻውን ነገር ሁሉ ማወቅ አልያም ልናውቀው የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ማወቅ እንችል ነበር፥ እኛ ከተሰወርንበት ክለላ (Chamber) ጋር እንኳ የማይገናኙ ነገሮች እንኳን ቢሆኑ። በምድር ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ነገሮችን ጭምር እናውቅ ነበር። ምድር ጨለማ ነበረች እንዲሁም በዚህ ሰማያዊ መቅደስና በምድር መሀከል ያለው ክፍተት ከሚገለጸው በላይ ጥቁር በሆኑ ደመናዎች ተሞልተዋል። በምድር ላይ እየሆነ ያለው ነገር ብቻውን አስቀያሚ ክፉና እኔ ውስን በሆነው የእኔ የሰዋሰው (የንግግር) እውቀት ልገልጸው የማልችለው አደገኛ ነበር። በአስገዳጅ (ከባድ) በሆነ ሁኔታ የተቀነሱ የሰው ዘር ብቻ ቀርቶ ነበር። ብዙዎች ብቻዋን በቀረች ምድር ላይ ሞተው ተኝተዋል። በጅምላ የተገደሉ ሰዎች በየቦታው ነበሩ። የምድር የተተወች ሆና የመቅረቷ እውቀታችን ሲጨምር፥ እንዲህ ብለን አሰብን፥ በሰው ዘር ታሪክ ሁሉ እንደዚህ ዓይነት ነገር ሆኖ አያውቅም። በማይነገር ሀዘን ውስጥ ከተተን። ያም ሆኖ፥ በሚገርም ፍቅሩና ጥበቡ ተውጠን፥ ይህ እውቀት በማንኛውም መልኩ ባከናወነው ነገር ሁሉ ከውዳችን ጋር የመሆንን ድንቅ ሊወስደው ይችላል?

በቶሎ ወደ ምድር ተመልሶ መግባትና የእውነተኛውን የእስራኤል **ንጉሥ** መመምጣት የሚጠባበቁትን እስራኤልን ሁሉና የተቀሩትን አሕዛብ ሁሉ የማዳን ጥሪ ምላሽ መስጠት እንዳለብን ስናውቅ ፍጻሜያችን (እጣ ፈንታችን) ልባችንን መቆጣጠር ጀመረ። እስራኤል በሙሉ እየጠበቀ ነበር፥ **መሚሐቸው** እንዲመጣና ነፃ እንዲያወጣቸው። ታላላቅ የእስራኤል ሕዝብ ከበርቴዎች **እ**ርሱ ብቻ ሊያድናቸው የሚቻለውን በፍጹም መሻት ሲፈልጉት። **መሚሕ** ሊያደርግ ያለውን ቅጽበታዊ አርነት ያውቅ ነበር። በሰዎች ልጆች ታሪክ ውስጥ ትክክለኛ ስፍራውን በምድር ላይ በመጨረሻ እንደ ንጉሥ የሚረከብበትን ይህን ጊዜ መጠባበቁ እየጨመረ ሲሄድ ይሰማን ነበር። መጠባበቁና ሀሴት ማድረጉ እያደገ ሲሄድ፥ የእኛም እንዲሁ ያድግ ነበር፥ እኛ ራሳችን አሁን ከምንወድደው ከ**እ**ርሱ ጋር ልባችን አንድ ሆኗልና። በዚህ ጊዜ ከሙሽራይቱ ጋር ጥልቅ ቁርኝነትን እያጣጣመ ነበር፥ **መንፈስ ቅዱ**ስና መላእክቱ ደግሞ አሁንም ድረስ በምድር ላይ ያሉትንና የ**እ**ርሱ የሆኑትን በጥንቃቄ እየተንከባከቡን ለመገለጡ እየጠበቋቸው ነው።

ቀጣዩ ጊዜ በሚመስል ሁኔታ፥ ጊዜው ነበር፥ ወደ ምድር የመውረጃው፥ ዙፋኑን መሸከም የእኛ ድርሻ ነበር። **መሚሐችን** ቀስ በቀስ በሆነው መውረዳችን ከፊት ይመራን ነበር፥ አሁንም ድረስ በግልጽ እይታ (በሥጋዊ ዓይን) ሳይታይ በደመና ውስጥ ሆኖ። በመቶሺሆች የአይሁድ ሕዝብ በጉጉት መምጣቱን እየተጠባበቁ። ሊያነግሡት ዝግጁ ወደ ሆኑ ሕዝቦች እየሄደ እንደሆነ በማወቅ፥ **መሚሕ** በታላቅ መግባት በፋራን ተራራ ሰማይ ላይ እስኪደርስ ድረስ መውረዱን ቀጠለ፥ በዚያም ጊዜ እኛ በተራራው ከፍታ ትይዩ መውረድ ጀመርን። **የዘላለም ንጉሥ**ና ታላቁ የቅዱሳን ሠራዊት ሲታይ እጅግ የከበረ ነበር፥ ይህን በመሰለ አንድም ምድራዊ ንጉሥ ባላየው አስደናቂ ስርዓት ተሞልቶ፤ **የክብር ንጉሥ** በንግሥና አጊጦ ለራሷ በሆነ ከ**እ**ርሱ የተዘጋጀላትን የከበረ ልብስ ከለበሰችው ሙሽራው ጋር እየመጣ። ከከበረችው ቤተክርስቲያኑ ጋር -- ጌጣጌጦቹን ለማስታወስ አይቻልም። ኦህ፥ ቃላት በቂ አይደሉም -- መጽሐፍት ሊጻፉ ይችላሉ ግን ይህን ታላቅ መለኮታዊ የዘመናት ክስተት እውነታ ሊነግሩት አይችሉም።

በጋራ በዮርዳኖስ ተራሮች ባሻገር ከነገሥታት ጎዳና ጥቂት ከፍ ብለን ተጓዝን። በሰማይ ላይ ተንሳፎ ከነበረው ተሸካሚ (palanquin = (ቃሬዛ) ዙሪያውን ከልል ያለው እንደ ቃሬዛ ሆኖ በእያንዳንዱ ማዕዘን አንዳንድ ሆኖ አራት ተሸካሚዎች የሚሸከሙት) የማይቆጠሩ ቅዱሳን ሠራዊት አካል(አባል) ስሆን በምንም ዓይነት ልዩ የለውጥ ሂደት ውስጥ ማለፌን አላስታውስም፥ ነገር ግን በሆነ መልኩ ያ ለውጥ ተከስቶ አሁን ከፍጥረት ሁሉ ታላቅ የሆነው ሠራዊት አካል ሆነናል። ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ፥ በአሞን፥ ቅዱሱ ሠራዊት አሁን በነጭ ፈረሱ ላይ ሆኖ በግልጽ በሚታየው **በመለኮት የሠራዊት አለቃ** እየተመራ። ስለእውነት በድል አድራጊነት ቅዱሳን ሠራዊቶቹን አስከትሎ እየጋለበ። ዞረን ቀጥታ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዝን፥ በምስራቅ በር በምንገባበት በኩል። **የዘላለም ንጉሥ -- ለማዳን ኃያል**፥ እንዲሁም የከበረቸው ቤተክርስቲያኑ መላዋን እስራኤልን ለማዳን የጉዞ አቅጣጫውን ቀየረ፥ ውዱ፤ እንዲሁም መምጣቱን የሚጠባበቁ። **የክርስቶስ**-ተቃዋሚ **ለታላቁ ንጉሥ**

*የሆነውን ለመውሰድ የሚቻለውን ሁሉ አደረገ፥ ነገር ግን በመጨረሻ በ**ዘላለም ንጉሥ** በራሱ ከዙፋኑ ተሻረ። ዓይኖች ሁሉ (**ጌታን**) አይተውታል፥እናም መምጣጡን የተጠባበቁት ሁሉ ወደዱት።*

**መሢሑ** ከቤተክርስቲያኑ ጋር ሲመለስ የሚያሳይ እጅግ የከበረ ራእይ ነበር።

**ተፈፀመ።**

## ተጨማሪ ጥቅሶች

**1ተሰሎንቄ. 4:15-18 በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።**

**ራእይ.1:7 እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥አሜን።**

**የሐዋርያት ሥራ 5:29-32 ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ:- ከሰው ይልቅ ለእግዚአበሔር ልንታዘዝ ይገባል። እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፤ ይህን እግዚአብሔር፥ ለእስራኤል ንስሐን የኃጢአትንም ስርየት ይሰጥ ዘንድ፥ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው። እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው።**

**ራእይ.20:11 ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም።**

**ይሁዳ.1:14-15 ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ። እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።**

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com